ሰላማዊ ሰልፎች በሚደረጉባቸው ጊዜያት የፀጥታ ኃይሎች ሰዎችን እንደሚደበድቡ ተዘግቧል። (ክፍል 2 ለን ይመልከቱ)። በጥር ወር 1996 ዓ.ም. ላይ የኦሮሞ ተማሪዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ላነሱት ተቃውሞ ፌደራል ፖሊስ የሰጠው ምላሽ 330 ተማሪዎችን መያዝ ነበር። የተያዙት ተማሪዎች ወደ ኮልፌ የፖሊስ ማሰልጠኛ አካዳሚ ተወስደው በሹል የተፈጨ ድንጋይ ላይ ለሰዓታት በባዶ እግራቸው እንዲሮጡ እና ተንበርክከው እንዲድሁ መታዘዛቸውን ዓለም አቀፋዊ መያዶች ዘግበዋል። የተያዙት ተማሪዎች በመጨረሻ ተፈትተው ለቀሪው የትምህርት ዓመት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተባረዋል።

በአካባቢው ዘገባዎች መሰረት ፣ በብዙ የኦሮሚያ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ቤቶች እና ዩኒቨርስቲዎች ፖሊስ ተማሪዎችን ፣ አስተማሪዎችን ፣ እና ወላጆችን ደብድቧል። በየካቲት እና መጋቢት ወራት 1996 ዓ.ም. በጥር ወር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተያዙትና በተባረሩት 330 ተማሪዎች ላይ የተወሰዱትን እርምጃዎች ተማሪዎች በመቃወማቸው በመላ ኦሮሚያ ረብሻ ተቀጣጥሎ ነበር። መንግሥት የተማሪዎቹን የተቃውሞ እንቅስቃሴ በአነግ የሚደገፉ ፀረ-ሰላም ወገኖች ያደረጉት እንቅስቃሴ ነው ቢልም፣ የተባለው ድጋፍ ስለመኖሩ ምንም ማስረጃ አላቀረበም።

በየካቲት 17/96 የአምቦ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ቤት አስተዳዳሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታገዱት ተማሪዎች አንባር ስላለባቸው ስጋት ተማሪዎቹ ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጣቸው በማስገደዳቸው ምክንያት ረብሻ ተነሳ። ፖሊስ ወደ ትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ በመግባት ብዙ ተማሪዎችን በመደብደብ በትኗቸዋል። በየካቲት 25/96 ዓ.ም. የአምቦ ሁለተኛ ደረጃ እና የአዲስ ከተማ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ተሰባስበው ወደ ከተማው መካከል ሲያመሩ የኦሮሚያ ክልል ፖሊስ አባላት ጠመንጃ ወደ ሰማይ በመተኮስ የበተኑዋቸው ከመሆኑም በላይ፣ ተማሪዎቹንም ደብድበዋል።

በመጋቢት 8/96 ዓ.ም. በደምቢዶሎ፣ ምዕራብ ወለጋ ፣ ኦሮሚያ ክልል ሰላማዊ ተቃውሞ ሲያደርጉ ከነበሩት ተማሪዎች በብዙ ደርዘኖች የሚቆጠሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ፖሊስ ደብድቧል። በነቀምቴም ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ፖሊስ መደብደቡን እና በደርዘኖች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን እና አስተማሪዎችን ለሳምንታት ማገቱን የአካባቢው ታዛቢዎች ዘግበዋል (ክፍል 1 መን ይመልከቱ)

በዓመቱ ውስጥ በርካታ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች በተከሰቱበት ወቅት የፀጥታ ኃይሎች ጋዜጠኞችን ደብድበዋል። (ክፍል 2 ሀን ይመልከቱ)።

ቀደም ባሉት ዓመታት ከነበረው በተለየ ሁኔታ ፣ የፀጥታ ኃይሎች የተለያዩ የሃይማኖት ቡድኖች አባላትን ስለመደብደባቸው ወይም ስለማሰቃየታቸው ምንም ዘገባዎች አልነበሩም።

በጥር 1995 ዓ.ም. አበበ ናቄን በደበደቡ እና ባሰቃዩ የፀጥታ ኃይሎች አባላት ላይ ፣ በየካቲት 1995 ዓ.ም. አየለ ልየውን እና ሃብታሙ ልየውን በደበደቧቸው ላይ በመጋቢት 1995 ዓ.ም. አንድ አስተማሪን በአዲስ አበባ በደበደቡት ላይ በጥቅምት 1996 ዓ.ም. ካሣ ዘውዴን እና ስንሻው ተገኝን በደበደቧቸው ላይ ፣ ወይም በጥቅምት 1996 ዓ.ም. ረታ ባየህን፣ አወቀ ተገኝን፣ ደረጃው አየሁን ፣ እና አለልኝ አያሌውን በደበደቧቸው ላይ ምንም እርምጃ አልተወሰደም።

በጋምቤላ ክልል መንደሮች ላይ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች በተደረጉበት ወቅት የሠራዊቱ አባላት አኙዋክ ሴቶችን አስገድደው ስለመድፈራቸው ዘገባዎች ነበሩ ። እጨዋይ ከተማ ፣ ጋምቤላ ክልል ፣ በአኙዋኮች ላይ ጥቃት በተከፈተበት ወቅት በታህሣሥ 1996 ዓ.ም. ወታደሮች በጠመንጃ አስገድደው ሁለት የአኙዋክ ሴቶችን ስለመድፈራቸው መንግሥት ምርመራ አላደረገም (ክፍል 5ን ይመልከቱ)። ይህ ጥቃት በሚታመኑ ምስክሮች የተዘገበ ነው።

ሚያዝያ 7/96 ዓ.ም. ማንነታቸው የልታወቀ ሰዎች በአምቦ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ቤት ላይ የእጅ ቦምብ በማፈንዳት በ 30 ተማሪዎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል። ከዚህ ከመጨረሻው ፍንዳታ ጋር በተያየዘ አሥራ አንድ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ሥር ማዋሉን ፖሊስ ገልጾ ነበር። በዓመቱ መጨረሻ ላይ ተጠርጣሪዎቹ በሙሉ በዋስ ተለቀው፣ ክሱ እንደተንጠለጠለ ነው።

በዓመቱ ውስጥ የጎሣ ግጭት ብዙ ጉዳት እና የጥቂቶችን ሞትም አስከትሏል።

የወህኒ ቤቶች እና ይዞ የማቆያ /የማገቻ/ ማዕከሎች ሁኔታ በጣም መጥፎ ከመሆኑም ባሻገር ፣ መተፋፈጉ በጣም አሳሳቢ ችግር እንደሆነ ቆይቷል። እስረኞች ለመኝታ

የሚሰጣቸው ሥፍራ ስፋት በአብዛኛው ለአንድ ሰው ከ 62 ካሬ ሳንቲ ሜትር ያነሰ ሆኖ ፣ በአንድ ክፍል እስከ 200 ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። የዕለት ምግብ ባጀት ለአንድ እሥረኛ 2 ብር ያህል ስለሆነ፣ ብዙ እሥረኞች የቤተሰብ አባላት በየቀኑ ምግብ እንዲያቀብሏቸው ያደርጋሉ ፤ ወይም በራሳቸው ገንዘብ በአካባቢው ምግብ ከሚሸጡ ይገዛሉ። የወህኒ ቤቶች ሁኔታዎች ጤናማ አልነበሩም፣ የህክምና ዕርዳታ ማግኘትም አስተማማኝ አልነበረም። ለወህኒ ቤቶች ጥገና ባጀት አልነበረም። በእርሻ ላይ እና የመካኒክ ሥራ መሥራትን ጨምሮ እስረኞች በወህኒ ቤቶች ግቢ ውስጥ መንቀሳቀስ እና ምንም ያህል ባልተደራጁ ቤተመጻሕፍት መጠቀም ይፈቀድላቸዋል። ለእስረኞች የሚላኩ ደብዳቤዎች በአማርኛ መፃፍ ስላለባቸው አማርኛ የማያውቁት በውጭ ከሚገኙ ዘመዶቻቸው ጋር ግንኙነት ለመፍጠር አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል። ሆኖም ግን በአጠቃላይ ይህ ክልከላ በግብር አልዋለም። በፖሊስ የማገቻ ማዕከላት ታጋቾች የኃይል ጥቃት ይፈጸምባቸዋል። በኦሮሚያ የታገቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ድብደባዎች እንደተፈጸሙባቸው እራሳቸው ማስረዳታቸውን ዲፕሎማቲክ ታዛቢዎች ዘግበዋል። በአጠቃላይ ጎብኚዎች የሚፈቀድላቸው ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ጎብኚዎች ተጋቾችን ማየትና ማነጋገር ይከለከላሉ።

በዓመቱ ውስጥ በበሽታ የተነሳ በወህኒ ቤት ጥቂት ሰዎች ሞተዋል። ሆኖም፤ በዓመቱ መጨረሻ ላይ በወህኒ ቤት ውስጥ ስለሞቱት ሰዎች ቁጥር ምንም አኃዛዊ መረጃ አልተገኘም። የወህኒ ቤት ሹማምንት እነዚህን በመሰሉ የማኞች ቁጥር ላይ ዘገባዎችን ለመስጠት ፈቃደኞች አልነበሩም ። ቢያንስ አንድ የጋምቤላ ፖሊስ መኮንን ከጎሣ ግጭት ጋር በተያየዘ ምክንያት በወህኒ ቤት ውስጥ ታስሮ ሳለ ሞቷል (ገጽ 5 ን ይመልከቱ)

የቀይ መስቀል ዓለም አቀፋዊ ኮሚቴ (ቀመዓአኮ) ለወህኒ ቤት ዳይሬክተሮች እና የጥበቃ ኃላፊዎች ፣ የጤና እና የአስተዳደር ኃላፊዎችን፣ ሰብዓዊ ክብርን፣ የሴቶች እና ሕፃናት አያያዝን፣ የታመሙ ታጋቾችን ማከምን ጨምሮ እስረኞችን በሚገባ ስለመያዝ የሚሰጠውን ሥልጠና በነሐሴ ወር አጠናቋል። በሕዳር 1996 ዓ.ም. ቀመዓአኮ በአገሪቱ በሙሉ ካለፈው የላቀውን ሁለተኛ ስልጠና ጀምሯል።

ሴት እስረኞች ከወንዶች ተነጥለው ለብቻ ይኖሩ ነበር። ሆኖም ፣ ወጣት ጥፋተኞች አንዳንድ ጊዜ ከጎልማሶች ጋር ታስረዋል። ዕድሜያቸው ከ 15 አመት በታች ለሆነ ወጣት ጥፋተኞች 1 ማረሚያ ቤት ብቻ ነበር። በዚያ ማረሚያ ቤት ሥፍራ

ያልተገኘላቸው ወጣት ጥፋተኞች ከጎልማሶች ጋር ታስረው ነበር። የፍርድ ሥርዓት ያልተጀመረባቸው ታጋቾች በአብዛኛው ከተፈረደባቸው እስረኞች ተለይተው ክስ እስኪመሰረትባቸው ድረስ በአካባቢ ፖሊስ ጣቢያዎች ወይም ውስን በሆነው የማዕከላዊ ምርመራ ማገቻ ሥፍራ በአዲስ አበባ ታግተው ነበር። እስረኞች እንደ ተፈረደባቸው ወደ ፌደራል እስር ቤቶች እንዲዛወሩ ሕጉ ይጠይቃል። ሆኖም፣ አንዳንድ ጊዜ ይህ ድንጋጌ በግብር አይፈጸምም።

ቀመሳአኮ በወህኒ ቤቶች እና በፖሊስ ጣቢያዎች ነፃ ክትትል እንዲያደርግ መንግሥት ፈቅዷል። የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችም ለወህኒ ቤት ሹማምንት በቅድሚያ በማስታወቅ ጉብኝት እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸዋል። የአፍሪካ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሚያደርጋቸው ጉብኝቶች አንዱን በሰኔ ወር በአገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች የሚገኙ እስር ቤቶችን ጎብኝቷል። ቀመሳአኮ በአጠቃላይ የፌደራል እና የክልል እስር ቤቶችን፣ የሲቪል ማገቻ ሥፍራዎችን እና የፖሊስ ጣቢያዎችን በአገሪቱ በሙሉ በዓመቱ ውስጥ ተዘዋውሮ በማየት በሺሕዎች የሚቆጠሩ ታጋቾች የሚገኙባቸውን ብዙ መቶ ጉብኝቶች አድርጓል። ቀመሳአኮ ሶስተኛ ወገን ሳይጨመር/ሳይኖር ከእስረኞች ጋር በየጊዜው እንዲገናኝ ተፈቅዶለታል። የአነግ ተዋጊዎች ናቸው ተብለው በጥርጣሬ የታገቱ የሚገኙባቸውን ወታደራዊ ማገቻዎች እንዲጎበኝ መንግሥት ለቀመሳአኮ ፈቃድ ሰጥቷል። እንደዚሁም በብሔራዊ ፀጥታ ምክንያት የታገቱ ኤርትራውያን እና የኤርትራ ተወላጆች የሆኑትን መጎብኘቱን ቀመሳአኮ ቀጥሎበታል።

ከሦር ወንጀሎች እና ከሽብርተኝነት ተግባር ግንኙነት አላቸው በመባል በልዩ አቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት የተያዙትን ታዋቂ ታጋቾች ዲፕሎማቶች እንዲጎበኙ መፍቀዳቸውን የመንግሥት ባለሥልጣኖች ቀጥለውበታል።

መ/ ከሕግ ውጭ ማሰር ወይም ማገት

ሕገ መንግሥቱ ከሕግ ውጭ ማሰርን እና ማገትን ይከለክላል። ሆኖም ግን በአሰራር ብዙ ጊዜ መንግሥት እነዚህን ድንጋጌዎች አያከብርም። የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ነው። የኋለኛውም በበኩሉ ለፌደራል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት/ፓርላሜንት፣ የአካባቢ መንግሥት ታጣቂዎች ፣ በአብዛኛው

ከፖሊስ እና ከሠራዊቱ ነፃ ሆነው እንደ አካባቢ የፀጥታ ኃይሎች ይሠራሉ። በፖሊስ ኃይል ዘንድ ፣ በተለይም ከአሸከርካሪዎች ጉቦ ይጠይቃሉ ተብለው በሚወቀሱት አንፃር ፣ አነስተኛ ጉቦኝነት ችግር እንደሆነ ቆይቷል። ማን አለብኝነትም ከባድ ችግር እንደሆነ ነበር። እነዚህን በመሳሰሉ የመብት ረገጣዎች ላይ ፖሊስ የሚያደርገው ምርመራ ውጤት በአብዛኛው ለሕዝብ አይገለጹም። ሆኖም፣ በግንቦት ወር አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስፍን ተቀባ የተባለውን የፖሊስ መኮንን ከታክሲ (ውይይት) አሽከርካሪ ጉቦ በመጠየቁ 4 ዓመት እሥራት በይኖበታል። የፌደራል ፖሊስ አባላቱ እና እንደዚሁም የክልል ፖሊሶች ሙያተኝነት እንደሚጎድላቸው አምኖአል ። በከፊል በዋነኛ ለጋሾች እገዛ የተደገፈ የማሻሻል ሂደት በዓመቱ ውስጥ ተጀምሯል።

በከፊል እዝና ቁጥጥር ስለተሻሸለ እና የተሻለ ሥልጠናም በመሰጠቱ ፣ በዓመቱ መጀመሪያ ረብሻዎች በተፈጠሩበት ጊዜያት በተለይም ሁከት በተባባሰባቸው አካባቢዎች የፖሊስ ኃይሎች መፋጠጥን በመተው እና የሚወሰዱትንም የአፀፋ እርምጃ በመመጠን፣ የረብሻውን መባባስ ማስቀርት ችለዋል ። እንደዚሁም የፖሊስ ኃይሎች ውጥረቶችን በቅድሚያ ለይቶ ማወቅን እና አፀፋቸውን ማፋጠንንም አሻሽለዋል።

መንግሥት ፖሊስን እና ምልምል ወታደሮችን በሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ወይም አጠባበቅ የማሰልጠን ጥረቱን ቀጥሎ የሰብዓዊ መብት ሥልጠናውን ከማሻሻል እና ሙያዊ ከማድረግም ባሻገር ከሕገ መንግሥቱ እና ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች አንዳንድ አስፈላጊ ክፍሎችን በመጨመር ሥርዓተ ትምህርቱን እንዲያጠናክርለት የቀመዓአኮን ዕርዳታ ጠይቋል። ቀመዓአኮ በመስከረም 800 ያህል ለሆኑ ግጭት ለሚደጋገምበት የኦሮሚያ አካባቢ መሪዎች ለ2 ቀናት የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ስልጠና ሰጥቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዐት ሕግ መሰረት አንድ የታገተ ሰው በ48 ሰዓታት ውስጥ ክሱ እንዲነገረው እና አብዛኛውም በዋስ መለቀቅ አለበት። ሰው መግደልን፣ በሀገር ክህደት፣ እና ሙሰኝነትን ለመሳሰሉ ወንጀሎች በዋስ መለቀቅ አልተፈቀደም። በአብዛኛው በዋስ ለመለቀቅ ዋስትናው ከብር 1,000 አስከ 10,000 በመሆኑ ፣ ይህም ከአብዛኛው ዜጋ አቅም በላይ ነበር። በከባድ ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች በዳኞች ትእዛዝ ፖሊስ ለ14 ቀናት ይዞ ሊያቆያቸው ይችላል። ምርመራው ካላለቀ ተጨማሪ 14 ቀን በዳኞች ትእዛዝ እየታከለ ምርጫው ይቀጥላል። በግብር ፣ በተለይም ራቅ ባሉ

ክልሎች ፣ ባለሥልጣኖች አዘውትረው ካለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያግታሉ፣ በ48 ሰዓታት ውስጥ ክስ አይመሰርቱባቸውም። ሰዎች በዋስ ከተፈቱም፣ እንደገና ወደ ፍርድ ቤት አያቀርቧቸውም። ከታወቀ የማገቻ ማዕከል ባነሰ ሥፍራ መታገትንም ሕጉ ይከለክላል። ሆኖም፣ በደርዘን የሚቆጠሩ ኋላ ቀር የማገቻ ማዕከሎች በየአካባቢው ስላሉ ፣ የአካባቢው የመንግሥት ታጣቂዎች ይጠቀሙባቸዋል። እራሳቸው በግላቸው የሕግ አማካሪ ማግኘት አቅማቸው ላልፈቀደላቸው ታጋቾችም ክሳቸው ፍርድ ቤት ሲቀርብ፣ መንግስት የሕዝብ ተከላካይ ጠበቆች አቁሞላቸዋል። እነዚህን የመሰሉ ታጋቾች በእገታ በቆዩበት ጊዜ ግን ከሕግ አማካሪያቸው ጋር መገናኘት ፣ ጨርሶ ተከልክለዋል ወይም በጥቂቱ ተፈቅዶላቸዋል።

በትናንሽ ከተሞች ሰዎች ዳኛ ፊት ሳይቀርቡ ለረጅም ጊዜ በፖሊስ ጣቢያዎች እንደሚታገቱ እና አንዳንድ ጊዜም እነዚህ ሰዎች የት እንደሆኑ ለብዙ ወራት እንደማይታወቅ ከተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ብዙ ዘገባዎች ነበሩ። በተቃዋሚዎች የፖለቲካ ስብሰባዎች በመሳተፋቸው ደጋፊዎቻቸውን የመንግሥት ታጣቂዎች እየደበደቡ ምንም ክስ ሳይመሰርቱ አግተዋቸዋል በማለት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዓመቱ ውስጥ በርካታ ቅሬታዎችን አስመዝግበዋል (ክፍል 1 ሐን ይመልከቱ)።

ዓለም እንየው ፣ ጌታ ምትኩ፣ እና ገበየሁ ምትኩ የሚባሉ አባላቱ የመኢአድ አባልነታቸውን አንሰርዝም በማለታቸው ፣ የመንግሥት ታጣቂዎች ሚያዝያ 19 ቀን በእነሴ ወረዳ አማራ ክልል ያገቷቸው መሆኑን መኢአድ ዘግቧል። ሚያዝያ 20 ቀን አምስት የመኢአፓ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እንዲያዙ የአነማይ ወረዳ ሹማምንት አዝዘዋል። ሚያዝያ 25 ቀን ፖሊስ ሙሉጌታ ዋሴን የመኢአፓን የመረጃ በራሪ ወረቀቶች በማደሉ በመጨራ ከተማ ፣ ፈንታሌ ወረዳ ሰሜን ሸዋ አማራ ክልል ይዞታል።

እንደዚሁም የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ (ኦብኮ) አባል የሆነውን ኦልባና ሌሊሳን አነግን ይደግፋል ብሎ በመጠርጠር ፖሊስ እንዳሰረው ተዘግቧል። ፖሊስ ሰውዬውን ሁለት ወር ያህል ከሚሆን ጊዜ በኋላ ሐምሌ 13ቀን ከመፍታቱ በፊት በተፋፈገ ክፍል አቆይቶታል። በዘገባዎቹ መሰረት ኦብኮን በይፋ እንዲያወግዝ እና ከኦነግ ጋር እንዲያይዝው ፣ እነዚህን በማድረግም ከፖሊስ ማዋከብ እንዲላቀቅ ፖሊስ ሊያስገድደው ሞክሯል።

የዲሞክራሲያዊ ለውጥ ንቅናቄ የሚባለው ኤርትራያዊ ተቀዋሚ ቡድን ሶስት ኤርትራውያን አባላት የኢትዮጵያ ኤርትራ የድንበር ኮሚሽንን ውሳኔ በመደገፋቸው በ1995 ዓ.ም. ከታሰሩ በኋላ እስከ ዘገባው ዓመት መጨረሻ ምንም ተጨማሪ መረጃ አልነበረም።

የተቃዋሚው የመኢአድ አባላት ናቸው የተባሉ 200 ሰዎች ሚያዝያ 12 ቀን በሰሜን ሸዋ ደብረ ሲና ወረዳ ተይዘው የማስደንገጫና የማስፈራሪያ ቅጣት ከተሰጣቸው በኋላ ተለቀዋል። የፓርቲው አባላት እና የሰሜን ሸዋ ነዋሪዎች የሆኑት መርሻ ኃይሌ ፣ ወሰኔ ግዛው፣ ግሩም ታደሰ እና ምንዳ ግዛው ከ7 እስከ 30 ቀናት ለሆነ ጊዜ ባልታወቀ ምክንያት በእስር ቆይተዋል።

በዓመቱ ውስጥ መንግሥት በተለይም በኦሮሚያ እና በትግራይ መምህራንን ማዋከቡን ቀጥሏል። ነፃው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) በርካታ መምህራን አፍቃሪ አነግ ናቸው በመባል መታገታቸውን እና ብዙዎቹም እስከ ዓመቱ መጨረሻ በእስር ቤት መሆናቸውን ዘግቧል። አንዳንድ መምህራን ክስ ሳይቀርብባቸው ለአያሌ ዓመታት እንደታገቱ ይገኛሉ። እነዚህን በመሳሰሉ ሁኔታዎች ከ10 እስከ 15 ጊዜያት በእገታ የመቆያው ጊዜ ለ2 ሳምንታት እየተራዘመ ፍርድ ቤቶችም ፖሊስ ምርመራውን ለወራት እንዲቀጥል ፈቅደዋል። በተጨማሪም ዳኞች ከአንድ ጉዳይ ወደ ሌላ ይዛወራሉ፣ በቀነ ቀጠሮው በችሎት አይገኙም ፣ ወይም የተመደቡት ዳኞች በማጓደሉበት ወይም በሚሞቱበት ጊዜ አዲስ ዳኞች አይመደቡም። በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ያለው አቅም ማጣት ለዚህ ችግር አስተዋፅኦ ያደረገ ቢሆንም ፣ የብዙዎቹ የተራዘሙ እገታዎች መንስዔ ፖለቲካዊ እንደሆነ ይጠረጠራል። በመላው ኦሮሚያ በትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ነውጥ በተከሰተበት ጊዜ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን እና መምህራንን የአነግ ደጋፊዎች ናቸው በሚል ጥርጣሬ ፖሊስ ለሳምንታት አግቶአቸዋል (ክፍል 1 ሀን ይመልከቱ)። ለምሳሌ በመጋቢት 24 ፖሊሶች በቡራዩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሆለታ፣ ኦሮሚያ ክልል አስተማሪ የሆነችውን ዓለሚቱ ብሩን ካለፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ከ3 ሳምንታት በላይ አግተው ከማንም ጋር እንዳትገናኝ አድርገው እንዳቆዩዋት ተወስቷል።

ፖሊሶች ወደ ግል መኖሪያ ቤቶች እየገቡ ካለፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ሰዎችን ይይዛሉ ። መጋቢት 29 ቀን ፖሊሶች በደብረዘይት ፣ ኦሮሚያ ክልል ፣ ካለፍርድ

ቤት ትዕዛዝ ወደ 11 መምህራን ቤት ገብተው ቤቶቻቸውን በርብረው ፣ በኋላም እነዚያኑ 11 መምህራን ክስ ሳይመሰርቱባቸው ለአያሌ ሳምንታት አግተዋቸዋል። ሚያዝያ 1 ቀን በኦሮሚያ ክልል፣ በጉደርና በአምቦ ከተሞች ፖሊሶች በአብዛኛው መምህራን ወደ ሆኑ 60 ሰዎች ቤቶች የአነግ ደጋፊዎች ይሆናሉ በሚል ጥርጣሬ ገብተው በርብረዋል። ቤቶቻቸው የተበረበሩባቸው መምህራን ሞሲሳ ፉታሳን ፣ አበበ ጭምዲን እና ዲንሳ ሰርቤሳን ይጨምራሉ።

የተያዘ ግለሰብ በዋስ እንዲለቀቅ ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትዕዛዝ የፖሊስ ሹማምንት አያከብሩም፣ ለምሳሌ በሐምሌ 15 እና 16 የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሜጫ እና ቱለማ ማህበር (ሜቱማ) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን በዋስ እንዲለቅ ፖሊስን አዘዘ። የሜቱማ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ደርቢ ደምሴ፣ ገመቹ ፈየራ ፣ ስንታየሁ ወርቅነህ፣ ዳባስ ዋቅጅራ፣ እና ሽፈራው አንሰርሙ ከሁለት ወር በላይ ታግተው ቆይተው፣ በ10,000 ብር ዋስትና በነሐሴ 4 ተለቀው ነበር። ነገር ግን የግል ንብረታቸውን ለመሰብሰብ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተመልሰው በሄዱበት ጊዜ ፖሊስ ገመቹን እና ስንታየሁን መልሶ አሥሯቸዋል። ደምሴ ፣ ፈየራ ፣ ወርቅነህ እና ዋቅጅራ በዓመቱ መጨረሻ (በታህሣሥ) በዋስ ተፈተዋል። ሆኖም፣ አንሰርሙ ለሥራው ወደ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሲያመራ እንደገና ተይዞ ታስሯል።

በዓመቱ ውስጥ ፖሊስ ጋዜጠኞችን አግቷል። (ክፍል 2 ሀን ይመልከቱ)
ሰዎች ስብሰባዎች እና ሰላማዊ ሰልፎች በማድረጋቸው ፖሊስ አግተዋቸዋል። (ክፍል 2 ለን ይመልከቱ)

በልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ከተያዙት ጉዳዮች አንዳንዶቹ በፖለቲካ ምክንያት ነው በማለት ተቃዋሚ ቡድኖች ያሰሙትን መንግሥት አስተባብሏል (ክፍል 1 መን ይመልከቱ)።

ከሱማሊያ እና ከኬንያ በመንቀሳቀስ ለሚያጠቁት የታጠቁ ተቃወሚ ቡድኖች አፀፋ በመስጠት ፣ ሠራዊቱ በወሰን አካባቢዎች መንቀሳቀሱን ቀጥሏል። በጣም አብላጫ የሆኑት የሰራዊቱ ጣልቃ ገብነቶች በጋምቤላ፣ በሱማሌ፣ እና በኦሮሚያ ክልሎች የተደረጉት ናቸው። በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ወቅት አንዳንድ ጊዜ እገታዎች መደረጋቸውም ተዘግቧል።